# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ትግል

## ለምን? ወደየት? እንዴት?

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የተዘጋጀ መግለጫ

ህዳር 1963

ይህችን ጽሁፍ የምታነብ ኢትዮጵያዊ ተማሪ ወይም ም
ሁር ፣ አገርህን ወዳድ እንደሆንክ እንጠራጠርም፡፡ያገርህ
ድህነት፡የወገንህ በበሽታ መሰቃየትና የድንቁርና እስረኛ
መሆን እንደሚያበግንህ እናምናለን፡፡አገርህ እንድትሸሸል፡
ህዝብህ በሰላም፡በደስታ እንዲኖርና የእውቀት ብርሃን እን
ዲከፈትለት መሸትህ ከጥያቄ አይገባም፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች አሰቃቂ የሆነው ጊዜያዊው የኢት
ዮጵያ ሁኔታ እንዲለወጥና አዲስ ህዝባዊት ኢትዮጵያ እንድ
ትመሰረት መታገል ከጀመሩ ቆየት ብለዋል፡፡በዚች አጭር ጽ
ሁፋችን አማካይነት ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግልና አለማ
ለተማሪና ለምሁር በጭሩ ልንገልጽ እንወዳለን፡፡

አንዳንድ ነገሮችን በቅድሚያ ማብራራት ጠቀሳሳውን ሀ
ተታ በበለጠ ያብራራዋል ብለን እንገምታለን፡፡

1 ኢትዮጵያዊ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እናብራራ፡፡
ኢትዮጵያዊ ስንል የምንመለከተው የኢትዮጵያ ዜጋ መ
ሆንህን ብቻ አይደለም፡፡ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ —
ከጋላው፡ከትግሬው፡ከአማራው፡ከወላሞው፡ በበሚ
ን፡በደቡብ፡በምስራቅ፡በምእራብ ኢትዮጵያ ከሚኖረው
ህዝብ — ጋር አንድነትህ እንደሚሰማህ እንገምታለን፡፡
እንዲሁም ኢትዮጵያ የአፍሪካና "የሶስተኛው አለም"
ክፍል እንደመሆኗ መጠን የነዚህ ህዝቦች ችግር ችግ
ርህ፡የነሱ ጠላት ጠላትህ መሆኑን ትገነዘባለህ ብለ
ን እናምናለን፡፡

2 አብዛኛው ህዝብ መሃይምን በሆነበት አገር አንተ ተ
ማሪ ወይም ምሁር በመሆንህ ታሪክ የጣለብህ ከፍተኛ
አደራና ህዝብህን ለማገልገል የሚኖርብህ ልዩ ሀላፊ
ነት ይሰማሀል ብለን እንገምታለን፡፡አንተ የተቀዳጀ
ኸውን ጠቃሚ ትምህርት ለማስገኘት — ትምህርት ቤቶ
ን ለማስራት፡አስተማሪዎችን ለመቅጠር፡መጻህፍትን ለ

መግዛት... — ታታሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥሯል:ግሯል::ደሙን የሚመጥጡትን ተበዮች ተሸክሞ ከመኖሩም በላይ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ አንተን ለማስተማር ሳቡን አንጠፍጥፎአል::በአንተ እድሜ ብቻ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ጥረት:ግረት አሸንፎአቸው በጭር እድሜ ተቀጭተዋል:ወይም የስራ ፍሬያቸው ከአፋቸው ሲነጠቅ የሚበሉት አጥተው በረሃብ ረግፈዋል::ለዚህ ህዝብ ባለእዳ መሆንህን ትገነዘባለህ:ላብአደሩ ህዝብ ወሮታህ ከበዱ መሆኑ ይሰማሀል ብለን እንገምታለን::

3 አገርህን ወዳድ ነህ በሚል እምነት የህዝብህ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ትመኛለህ ብለን እንገምታለን::ድህነት:ድንቁርናና በሽታ ያገርህን ህዝብ ጥሰው እንዲጠፉ መፈለግህ አይጠረጠርም::አገርህ ለብበና አሸብርቃ:ያገርህ ህዝብ ደልቶትና ተደስቶ ቢኖር ትወዳለህ::ነገን የሀገራችንን ሁኔታ ስትመለከተው ሀብታምና ለምለም በሆነችው ኢትዮጵያ ህዝቡ በአስቃቂ የኑሮ ደረጃ ሲኖሩ ታየዋለህ::ይህ ባያስገርምህና "ለምን" ብለህ ራስህን እንድትጠይቅ ባያደርገህ አይቀርም::

አገራችን በሬና የተሰበጣጠረ የተፈጥሮ ሀብት አላት::ግን የኢትዮጵያ ህዝብ በድህነት ይጉሰቆላል::የእያንዳንዱን ህዝብ የአመት ገቢ በገንዘብ ቢገመት ያብዛኛው ህዝብ ገቢ ከቶጥርም አይገባ::በየጊዜው ብዙ ህዝብ በረሃብ እንደሚያልቅ የታወቀ ነው::ዛሬ አውቀት በተስፋፋበት ዘመን በብዙ አገሮች የጠፉ ከበዱና ቀላል በሽታዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በሰፊው ይገኛሉ::ተስቦ:ፈንጣጣ:የሳምባ በሽታና ቁምጥና ህዝቡን ያስቃዩታል::በየአመቱ ከሚወለዱት ህጻናት ከግማሽ በላይ ሁለት አመት ሳይሞላቸው ይረግፋሉ::ዛሬ አለም በእውቀት ተትረፍርፋ ባለ ከህዝቡ 95 በመቶ ገደማ ማ



ንበብና መጻፍ አይችልም::የትምህርት እድሜ ካላቸው ህጻናት ለ5 በመቶው እንኳን ቦታ የለም::

የማንንም አገር ሁኔታ ልብ ብለህ ብትመለከት በዚህ የተሻለ ሆኖ ታገኘዋለህ::የዚህ ሁኔታ ምክንያቱ ምንድን ነው? ይህንንስ ሁኔታ እንዴት መለወጥ ይቻላል? ብለህ ራስህን መጠቀህ አይቀርም::

ከብዙ አመታት ጀምሮ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት እንደዋና ተግባር አድርገው የወሰዱት የነዚህን ጥያቄዎች መልስ ማወቅና ማሳወቅ ነው::የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት በየጊዜው የሚወስዱዋቸው የተጋድሎ እርምጃዎች ለነዚህ ጥያቄዎች ከገኙት ተጨባጭ መልሶች የፈለቁ ናቸው::የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ብዙ መንገድ ተጉዘዋል::የኢትዮጵያን ሁኔታ ለመረዳት:በአስተያየት ለመጉልመስ:በቆራጥነትና በመስዋእትነት ለመታገልአሁን ከደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ ያለፉዋቸውን ልዩ ልዩ ደረጃዎች መዘርዘር ብዙ ትምህርት ያስገኝ ነበር::በዚህ አጭር ጽሁፍ ውስጥ ይህንን ዝርዝር መስጠት ስለማንችል ታሪኩን ወደጎን ትተን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ዛሬ የቆሙበቸውን መሰረታዊ አላማዎችና የተደራጁበትን ዘዴ ለማብራራት እንሞክራለን::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት መሰረታዊ አላማ:—

"በኢትዮጵያ:በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ያሁኑ ንጉስ ነገስት መንግስት ስርአትና ኅብረተሰባዊ አቋም ከስረ መሰረቱ እንዲለወጥ ይታገላሉ::ለኢትዮጵያ ህዝብ ድህነት:ድንቁርናና ህመምተኛነት ዋና ምክንያት የሆነው የንጉስ ነገስቱ አገዛዝና ያለው ኅብረተሰባዊ አቋም ነውና::በዚህም ስርአት መቃብር ላይ የህዝብ ነጻነት:አንድነትና እኩልነት የሚከበርበት:ደህንነቱ የሚረጋገጥበት አዲስ ስርአት እንዲገነባ ይታገላሉ::"

እንዴት? ነገሩን የምንመለከተው ባጭሩ እንደዚህ ነው::

የኢትዮጵያ ህዝብ የረጅም ጊዜ ትግል አለው::ይህም ታሪክ የነገስታት መውረድና መውጣት ታሪክ ብቻ ሳይሆን ህዝባችን ጭቆናን በመቋቋም ለነጻነቱ፣ለክብሩና ለሀገሩ በአስደናቂ ጀግንነት ሲዋጋና ሲሰዋ በላቡና በደሙ የጻፈው የሚያኮራ ታሪክ ነው::

ትውልዳችን በዚህ ታላቅ የታሪክ ቅርስ ከልቡ ሊኮራበት ይገባል::ይኮራበታልም::ነገር ግን "የአባት ዘራፍ ለልጁ አያልፍ" ይባላል::በአባቶቻችን ታሪክ ብቻ እየኮራን እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ አንችልም::ጊዜያዊ ተግባር አለብን:: ከዚህ አኩሪ ታሪካችን ጋር የተያያዘ፣ከሁሉም በቀጥታ የፈለቀና በዘመኑም የኢትዮጵያና የአለም ሁኔታ የሚወሰን አዲስ የታሪክ አደራ አለብን::

የኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነት ትግል ገና ከታሰበው ግብ አልደረሰም::በዙሪያችን ዘወር ወር ብለን ብንመለከት ከብዝበዛ አፍዩ ብሎ የማያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ከመቸውም ይበልጥ በረሃብ ሲገረፍ፣በበሽታ ሲቀጣ፣በድንቁርና ሲታፈን እናያለን::በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የሚሰቃዩ በአለም ብዙ ህዝቦች አሉ::እነሱም በያለበት የዚህ አሰቃቂ ሁኔታ ምክንያት የሆኑትን የባእድም ሆነ የሃገር በዝባዦች በመቋቋም ላይ ይገኛሉ::ይህ ዛሬ በመላው አለም — በኢትዮጵያ ጭምር — በጥቂት በዝባዦችና በሰርቶ አደር ተበዝባዥ ህዝቦች መካከል የሚደረገው ታላቅ ትንንቅ ለዘመኑ አይነተኛ መልክ ከሚሰጡት ተጋድሎዎች አንዱና ዋናው ነው::

ይህ ትግል በሚካሄድበት ወቅት በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ — በተለይ በተማሪውና በምሁሩ — ላይ የሚወድቅበት ታላቅ የትግል አደራ ገለልተኛ ነኝ እያሉ እንደሰጎን አይን መጨፈን አይደለም::ከዘራፊዎችም ተደባልቆ መዝረፍ አይደለም::ከተበዝባዦች ተደባልቆ ለመራራ ለቅሶአቸው ሙሾ ማውረድ አይደ



ለም::የትውልዳችን ዋና አደራ ህዝባችን በረጅም የነጻነት ትግል ታሪኩ ደጋግሞ ባፈራቸው ተጋዳዮች አርአያነት በመመራት የኢትዮጵያችንን የእውነተኛ ነጻነት ቀን ለማብሰር ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር ተደባልቆ ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር መሰለፍ ነው::

የትግሉ መነሾ ምንድን ነው?

በሀገራችን ታሪክ — በአለምም ታሪክ ቢሆን — የጥቂቶች መትረፍረፍና የብዙሀን ማጣት፣የጥቂቶች መብለጭለጭና የብዙሀን መራቆት፣የጥቂቶች የተሟላ ኑሮ ፍስሀና የብዙው ህዝብ ቀጥና ትርጉም ያጣ የኑሮ ፈተና ከመቸውም ይበልጥ ዛሬ አይን አውጥተው ጎን ለጎን ይኖራሉ::በዚህ አንጻር ደግሞ በሰው ልጅ ወዝና ምርምር የተከማቸዉ እውቀት ሰርቶ አደሩ ህዝብ የተሟላ ኑሮ እንዲኖር እንደዛሬም በሬ እድል ከፍቶለት አያውቅ::ነገር ግን አንዳንዱ የአለም ህዝቦች በቆራጥ ትግል ያገኙት ይህ ታላቅ እድል በኢትዮጵያችን በጥቂት በዝባዦች የግል ጥቅም አገልጋይነት በመሰናከሉ ለሀገራችን ህዝብ እስከዛሬ ተነፍጎታል::

ስለዚህም ሌሎች ህዝቦች ጨቋኞችን እየደመሰሱ የዘመኑን እውቀት ለተሟላ ኑሮአቸውና ከትውልድ ትውልድ ለሚያልፍ ቁም ነገር ሲያውሉት የኢትዮጵያ ህዝብ በጊዜው ስልጣኔ ያተረፈው ቅንጣት ነገር ቢኖር የተራቀቀ የጭቆና አገዛዝ ዘዴ፣አደናቋሪ ፕሮፓጋንዳ፣አለም በቃኝ፣የመርዝ ጢስ፣የጥይት ዝናብና የቦንብ በረዶ ነው::የሚያስፈልገውን የእውቀት ብርሃን ሞራና የተሟላ ጤና ፍስሀ፣የሚገባው ወገና ነጻነት ያለው ኑሮ እስከዛሬ አላገኘም::

ይህ ነው የማይባል የተበበጨጠረ ሰብአዊና የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገራችን በአለም አቀፍ ከፍተኛ ቦታ መያዝ ስትችል ዛሬ የህዝቧ የተጎሳቆለ ኑሮ ከአካባቢዋ የአፍሪካ አገሮች ጋር እንኳን ሊነጻጸር አይችልም::በጣም ዝቅ ያለ ነው::

የዚህ ምክንያቱ ምን ይሆን? ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ጥቂት ሰዎች የሀገሬቱን መሬት በጉልትና በሰሞን፡ወይም በርስተ ጉልትና በርስት ስም የግል ሀብታቸው አድርገው፡ የሀገሬቱን ህዝብ በተገዥነት እጅ አገሩን ጠፍረው ይዘው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን የሚያፈሩት ምርት በመቶ ለሚቆጠሩ ገዥዎች የግል ጥቅም እንዲውል በመደረጉ ነው።

ከመሰፍንት ተወልደናል፤ከመኳንንት ተወልደናል፤የነጉስ ዘር ነን፤አበቴ ይህን ያህል ጢሰኛ አውርሶኛል እያሉ ሌሎችን እያሰሩ የሚኖሩትና አማካሪዎቻቸው በአንድ ላይ ተጠቃለው አንድ የህብረተሰብ ክፍል ናቸው። ይህም የህብረተሰብ ክፍል — መደብ እንለዋለን — ፊውዳሳዊ ወይም ባላባታዊ መደብ የሚባለው ነው። በሌላ ወገን ደግሞ የሰራውን ፍሬ በየምክንያቱ የሚዘረፈውና ለበዝባዦች እንዲያስረክብ በህግ የሚገደደው ገበሬና ሰራተኛ ህዝብ አለ። ይህ የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ የተበዝባዡ መደብ ነው። የፊውዳል ወይም የባላባት መደብ በሌሎች ትከሻ ላይ ተቀምጦ በፈላጭ ቆራጭነት የሚገዛበት ስርአት የፊውዳል ወይም የባላባት ስርአት ይባላል።

ማንም አእምሮ ያለው ሰው ሊያስተውለው እንደሚችል ሁሉ በእንደዚህ አይነቱ ስርአት ውስጥ በሰርቶ አዳሪው ህዝብና ተቀምጦ በሚገፈው የበዝባዦች መደብ መካከል ትልቅ የጥቅም ግጭት አለ። ይህም ትግል ያስከትላል።

በዚህ ትግል ውስጥ የገዥው መደብ "የንጉስ ነገስት መንግስት" በሚባለውና በቀንዳሞቹ በዝባዦች በሚመራው የበዝባዦች ወኪል ድርጅት ይጠቀማል። ይህ ወኪል ድርጅት ጦር ሰራዊቱንና ፖሊሱን በማደራጀት፡ሰላዮንና ፕሮፓጋንዳውን በያለበት በመንዛት፡በቤተክህነትና በቤተመስጊድ ስበከት በመጠቀም የበዝባዦችን ጥቅም ሲያጸድቅና ህዝብን ሲያሰድድ፡ሲገድል፡ሲያስርና ሲያጉስቁል ይታያል። የህዝቡም ወገን መጀመሪያ ላይ ተበታትኖ የተዳከመ ቢመስልም አለታዊ ትግሉን ከማካሄድ አያ



ቋርጥም። ህዝቡ በትግሉ ውስጥ ቀስ በቀስ እየተደራጀ እንደሚጠነክርና በዝባዦችን ደምስሶ ዱላን እንደሚጎናጸፍ ጥርጥር የለውም። ይህ በምንም አይነት ሊሸር የማይችል የታሪክ ህግ ነውና።

በዚህ መልክ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተጫነው የበዝባዦች ስርአት ዛሬ ብቻውን አይደለም። ከጥቂት ዘመናት ወዲህ አዲስ የዘረፋና የጭቆና ስርአት በሀገራችን ላይ ጥላውን በሰፊው ጥሏል። ይህም የበእድ ጭቆና ቀንበር ነው። የበእዳን ዘራፊዎች በሌላው አለም እንዳደረጉት ሁሉ አገራችንን በጦር ኃይል ለመያዝን ህዝባችንን በባርነት ለመግዛት ደጋግመው ሞክረው ነበር። ግን በዚህ መንገድ አልተሰከላቸውም። ይህን ማንም ያውቀዋል። ህዝባችን የማያውቀው ከጥቂት ጊዜ ወዲህ እነዚህ ባእዳን ከገዥው መደብ ጋር በጥቅም በመሸረከ በገልጽና በምስጢር እየተዋዋሉ በሀገራችን ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ቦታ መያዛቸውን ነው። በዚህ መልክ አገራችንን ሰርስረው የገቡት ባእዳን ዘራፊዎች ኢምፔሪያሊስቶች የምንላቸው ናቸው። በያዝነው ወቀት በኢትዮጵያና እንዲሁም በያለበት መርዘኛ ሰፉን በመስደድ የአለም ህዝብን በበለጠ የሚመጥጠው የአሜሪካኖች ዘረፋ ነው።

በዚህ መልክ ሀገራችን የበእዱ ዘራፊዎች መፈንጫ እንድትሆን በሩ በሰፊው በመከፈቱ ዛሬ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት ለበእዳን ባለገንዘቦች ጥቅም መዋል ጀምሯል። የሀገራችን ህዝብ ጉልበት ያለአንዳች ርህራሄ በበይተጥር ጉልበተ—በሎች ይበዘበዛል። የሀገራችን ነጋዴዎችና ባለፋብሪካዎች የእቃቻውን ስር ተው እንዳይዳብሩና ሀገራቸውን እንዳይረዱ መንገስቱ የሚያገዛቸው በእዳን ባለገንዘቦች አሳፈናፍነ ብለዋቸዋል። ይህን ሁሉ ግፍና ቀንበር አሜን ብለን እንድንቀበል በበእዳን የሚነዛው የበሀል ነቀርሰና አስከሬ ፕሮፓጋንዳ በራሳችን ያለንን እምነት እንድናጣ፡ማንነታችንን እንድንረሳ፡በሀሳችንን እንድናረክስና ኢትዮጵያዊነታችንን እንድንጠየፍ የማያደርገው ሙከራ የለውም። ይህ አገረ ወዳድ የሆነ ኢትዮ

ጵያዊ ሁሉ የሚያውቀውና የሚቆጭበት ድርጊት ነው።ከዚህም አ
ልፍ ተርፎ በአባቶቻችን ደምና አጥንት ታፍራ የኖረችው አገራ
ችን በሺህ የሚቆጠሩ የባእድ ወታደሮች ከነትጥቃቸው ሰፍረውበ
ት አናያለን።የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ሀገራችንን በኛም አ
ልፈው በአካባቢው የሚበዘበዙትን ህዝቦች ነቃናቂ የሚደቁሙበት
ጦር ማከማቻ አድርገዋታል።ስለዚህም ትናንት የነጻነት ፋናዋ
ን እያበራች ለአፍሪካ ህዝብ በሙሉ የመንፈስ ኩራት የነበረች
ው ሀገራችን ዛሬ የተገላቢጦሽ "የአሜሪካን የቅኝ ሠቀሰይ ገ
ዛት" ብላ የሀፍረት ስም ታተርፍ ከሸጡዋት ከሀዲዎች በስተ
ቀር የማይበገን ኢትዮጵያዊ የሚገኝ አይመስለንም።

እንደዚህ በተባበሩ ድርብ ጠላቶች ታፍኖ የኢትዮጵያ ህዝ
ብ እንኳንስ ወደፊት ሊራመድና በማንኛውም ረገድ ከአለም ህዝ
ቦች መጠረሽ የሆነውን የተጎሰቆለ ኑሮውን ሊጠብቅ አልቻለም።
ነገር ግን ከዚሁ ህዝብ ጉልበት በሚዘረፈውና አገር እንደእቃ
ተሸጦ በሚገኘው ሀብት ከሀዲዎቹ በዝባዦች የቅምጥል ኑሮአቸው
ን ሲያሙቀሱና ሀገራቸውን በየቀኑ ለባእዳን ይበልጥ አያሳለፉ
ሲሸጡዋት አናያለን።

ይህን ወደር የሌለው ብዝበዛ፡ጭቆናና ውርደት አይን አያ
የ፡ጆሮ አየሰማ መቀበል በኩሪው ታሪካችን ላይ የሚፈጸም ታላ
ቅ ወንጀል ነው ብለን እናምናለን።ስለዚህም እንደዚህ በየቀኑ
ህዝባችንን ከሀብቱ አየዘረፈ፡ከሰብአዊነቱ አየቆረሰ የሚያራቁ
ተውና የሚያዋርደው በከት የንጉሠ ነገሥት ስርአት እስኪሻርና
በቦታው የህዝብ ነጻነት፡እኩልነት፡አንድነትና ብልጽግና የሚረ
ጋገጥበት አዲስ ህዝባዊ ስርአት እስኪመሰረት ድረስ ማንም እ
ውነተኛ ኢትዮጵያዊ ምንም እረፍት ሊኖረው አይችልም።ማኅበራ
ችን የተጋዳዩን ህዝብ ወገን መርጦ በታላቅ መስዋእትነት ጠቋ
ኞችን የሚቋቋመው ለነዚህ ለነጻነት፡ለእርምጃ፡ለሀገርና ለወገ
ን በሚደረገው ትግል ታሪክ የጣለበትን አደራ ጠንቅቆ በመገን
ዘቡ ነው።

የትግሉ አላማ ምንድን ነው?

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለብዙ ዘመናት የሀገራችንን የተፈጥ



ሮና ሰብአዊ ሀብት በመመልከትና የህዝቡዋን መጉሰቁል በመገን
ዘብ፡ኢትዮጵያ ሳለችበት አስቃቂ ሁኔታ ዋና ምክንያት የሆኑት
ን ነገሮች በማጥናትና ይህስ ሁኔታ እንዴት ሊለወጥ እንደሚቻ
ል በመመርመር ብዙ የትግል ጉዳና ከተጓዙ በኋላ ዛሬ የሚታገ
ሉለት "የመሰረታዊ ለውጥ" አላማ ደርሰዋል።

ይህም አቢይ ይዘቱ እንደዚህ ነው።ጊዜው የሸረው የበሰ
በቱ ፊውዳላዊ መደብ ከባእድ ዘራፊዎች ጋር ገጥሞ መ
ላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እየተበበሰ በሚሄድ ጭቆና አፍኖ ይዞ
ታል።ማንኛውም ነጻነት፡ሰላም፡አንድነት፡እኩልነትና እርምጃ
ሊገኝ የሚችለው እነዚህ ጥንዱ የኑሮ መርዞች በህዝብ ኃይል
ከመሰረታቸው ሲነቀሉና በኢትዮጵያ አዲስ ህዝባዊ ስርአት ሲመ
ሰረት ብቻ ነው።አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
አላማ እንዲህ ይላል፦

"የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር፡የኢትዮጵያ ህዝብ ረሃብ፡የኢትዮ
ጵያ ህዝብ ድንቁርናና በሽታ ሊወገዱ የሚችሉት ያሁኑ አ
ገዛዝ ተጥሎ በገበሬውና በሰራተኛው ጥቅም ላይ የተመሰረ
ተ ህዝባዊ መንግስት የተፈጠረ እንደሆነ ብቻ ስለሆነ ይ
ህ መንግስት በፍጥነት እንዲመጣ በቆራጥነት መታገል።"
— አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ህገ ማኅበ
ር፡ምእራፍ 1፡ቁጥር 1።

ዘር ዘር ይህ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ከህዝቡ ትግል
የሚለይበት ምንም ነገር የለውም።ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚ
ታገለው ከማንኛውም ጭቆና ተላቅቆ ለነጻነትና ለእርምጃ ያደረ
በትን ትክክለኛ ጉጉት ለማርካት ነው።የኢትዮጵያ ህዝብ በዚ
ህ ትግሉ ከሚገበው አልፎ የሚጠይቀው ቅንጡት ነገር የለውም።
ይህ አላማ ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን ታታሪው የኢትዮጵያ ህዝ
ብ በነጻነት፡በአንድነትና በሰላም በወዙ ኑሮውን እያሻሻለ ለ
መኖር የሚችልበት አዲስ ህዝባዊ ስርአት ለመፍጠር ነው።ይህ
ም የተሟላ ኑሮ ከማንም በጎ አድራጊ የሚለገስ ችሮታ ሳይሆ
ን በሰላምና በሀብታም አገራችን የሚፈሰው የህዝብ ላብ ከዘ
መኑ ጥበብ ጋር ተዋህዶ የሚያፈራው የኑሮ ፍስሀ ነው።

ከዚህ በፊት በየጉባኤውና በልዩ ልዩ ስብሰባዎች በተደረጉት ውሳኔዎች ላይ በመመርኮዝ የተማሪዎችን ዋና ዋና አላማዎች እንደሚከተለው መደርደር ይቻላል:—

1 የጊዜው የንጉስ ነገስት መንግስት ተደምስሶ በሱ መቃብር ላይ ከበሳበት ጭቆናና ከበእዱ ብዝበዛ የተላቀቀ:የህዝብን ነጻነት:እኩልነት:አንድነት:ሰላምና ብልጽግና የሚያረጋግጥ ህዝባዊ መንግስትና ህዝባዊ ስርአት እንዲቋቋም እንታገላለን::

2 የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲዳብርና የህዝቡም የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲል የሚደረገው ከፍተኛ ጥረት በተደራጀ መልክ እንዲታቀድ:እንዲቀናበር:እንዲመራና ሰፊው ህዝብም ሊሳተፍበት እንዲችል እንታገላለን::ለዚህም:—

ሀ. በእርሻ በኩል የገበሬዎችን ኑሮ ለማሻሻል "መሬት ላራሹ" የሚለውን አላማ ስራ ላይ ማዋል፤ከንጉሳዊ ቤተሰብና ከታላላቅ ባለመሬቶች መሬትን በነፃ በመውረስ በቂ ወይም ምንም መሬት ለሌላቸው የገበሬ ቤተሰቦች ማከፋፈል::የግል መሬታቸውን እያረሱ የሚኖሩ ገበሬዎችን መብት መጠበቅ::ለሁሉም አስፈላጊውን እርዳታና ምክር መስጠት::ገበሬዎች እየተረዳዱና እየተደጋገፉ በደቦ መልክ በመስራት የጋራ ጥቅማቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር::መንግስቱ በበኩሉ ታላላቅ ዘመናዊ እርሻዎችን የህዝብ ሀብት በማድረግ የጋራ ሀብትን ማስፋፋት ግዴታው ይሆናል::

ለ. በኢንዱስትሪ በኩል የሀገሪቱ የተበጠጠሩ የጥሬ እቃዎች መሰረት እንዲደከምበትና ለወደፊት ብልጽግናችን ዋስትና የሚሰጠን የከበዱ ኢንዱስትሪ መሰረት እንዲጣልና እንዲገነባ:ቀላል ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ፤የሰራተኞችን መብትና ደህንነት ለማረጋገጥ ጥበቃ ህግ እንዲደነገግና ስራ አጥ ተው የሚቸገሩ ሁሉ እንደ



የችሉታቸው እየሰሩ ራሳቸውንና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ መደረግ አለበት::

ሐ. በንግዱ በኩል ሀገራችን እንድትበለጸግ የሀገሩን ነጋዴዎች ማበረታታትና ማገዝ ታላላቅ የንግዱ ቤቶችን ከመንግስት እጅ በማስገበት የህዝብ ሀብት ማድረግ ያስፈልጋል::

3 ለህዝብ እድገትና ለተሟላ ኑሮ የሚያገለግል:ለህዝብ ልጆች በሙሉ የሚደርስ ነጻ ትምህርት እንዲስፋፋ:መሃይምነት እንዲጠፋ:ሰይንስ:ስነጥበብና ስነጽሁፍ እንዲደረጁ:የሀገሪቱ ልዩ ልዩ ባህሎች ዘመኑ ከፈራቸው እውቀት ጋር እየተዋሀዱ እንዲበለጽጉና እንዲራመዱ እንታገላለን

4 የህዝቡ የተሟላ ኑሮ እንዲረጋገጥ ጤናው የሚጠበቅበት:ዱኩማን የሚረዳበት:ጥዋሪ ያጡ ሽማግሌዎች የሚጦሩበት:ሰብሳቢ ያጡ ህጻናት በወግ የሚያዱጉበት:በጭሩ ህዝባችን በቆየ ልምዱ መሰረት እርስ በእርሱ እየተረዳዳና እየተደጋገፈ የሚራመዱበቸው ድርጅቶች እንዲስፋፉ እንታገላለን::

5 የህዝቡ መሰረታዊ ነጻነቶችና ሰብአዊ መብቶች እንዲጠበቁና ትክክለኛ ፍትህ እንዲሰፍን፤በዚህም መሰመር የመጻፍ:የመሰብሰብ:የሰላማዊ ሰልፍ:የእምነት... ነጻነቶች የተረጋገጠ ዋስትና እንዲሰጣቸው እንታገላለን::

6 በሃይማኖት:በጾታ:በነገድ:የሚደረገው ልዩነት ፈጽሞ እንዲጠፋና እኩልነት:አንድነትና ሰላም እንዲሰፍን፤ለዚህም በተለይ በነገዶች ጉዳይ በሀገሪቱ የሚገኙት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች:ባህሎችና የኑሮ ዘዴዎች በእኩልነት አይን እንዲታዩና እንዲበለጽጉ እንታገላለን::

7 የአለም ተበዝባዥ ህዝቦች ለነጻነት:ለእርምጃና ለሰላም

የሚያደርጉትን ትግል ትክክለኛነት በመረዳትና ትግላቸው ትግላችን መሆኑን በመገንዘብ ከነዚህ ህዝቦች ጋር በአንድነት ጸረኢምፔሪያሊስት ትግላችንን እንቀጥላለን::

አላማችንና እምነታችን እነዚህ ናቸው::እነዚህን መሰረታዊ አላማዎች ከስራ ላይ ለማዋል የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቆርጠው ሲታገሉ ብዙ ጊዜ ሆኖአቸዋል::ለዚሁም ብዙ ሀገረ ወዳድ ወጣቶች የታሰሩበት፡የተገረፉበትና የተሰደዱበት ቢሆን ብዙ ወጣቶች ደግሞ የመጨረሻውን መስዋእትነት በመቀበል ህይወታቸውን ለሀገራቸው አሳልፈው የሰጡበትና በደማቸው የጻፉዋቸው የተቀደሱ አላማዎች ናቸው::

እነዚህ አላማዎች ያለመሰረታዊ ለውጥ ሊፈጸሙ እንደማይችሉ ግልጽ ነው::መሰረታዊ ለውጥ ያለመራራና ቆራጥ ህዝባዊ ትግል አይገኝም::ይህም ቆራጥ ትግል በደንብ የተደራጀ እንጂ የእውር ድንበር መሆን የለበትም::በደንብ የተደራጀ ግንበር ቀደም ህዝባዊ ድርጅት ያስፈልጋል::ይህንንም አስፈላጊ ሕዝባዊ ድርጅት ለመፍጠር መታገል ያስፈልጋል::ትግሉ ሰፊና እንደ ሰንሰለት የተያያዘ ነው::ረጅም ጊዜ ይወስዳል::

ይህን ትግል ለማካሄድ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በምን አይነት ዘዴ ተደራጅተዋል?

## የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ድርጅት

ትምህርት በኢትዮጵያ ያልተስፋፋ ስለሆነ በተለይ በከፍተኛ ትምህርት የተማሩ ተማሪዎች ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚገኙት ከ3000 አይበልጡም::በውጭ አገር 1500 ያህል ይገኛሉ::በውጭ አገር ካሉት በብዛት የሚገኙት በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ቢሆን በነዚህ ቦታዎች የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ተቋቁመዋል::በኢትዮጵያ የሚገኙትም ከብዙ ትግል በኋላ በ1962 — እአአ — ብሄራዊ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ለማቋቋም ችለዋል::በኢትዮጵያ፡በአውሮፓና



በሰሜን አሜሪካ የሚገኙት የኢትዮጵያ ተማሪዎች በማኅበሮቻቸው አማካይነት የኢትዮጵያን ሁኔታ በመመርመርና በመረዳት ከላይ የዘረዘርነውን አቋም ተከትለው መታገል ከጀመሩ ከአምስት አመት በላይ አልፎአቸዋል::የበሰቱን ማኅበራት አንድነት ለማጠንከር፡ ትግል ለመምራትና ለማቀናበር በ1967 — እአአ— አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተመሰረተ::

## 1 አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

አባል ማኅበራት፡— ብሄራዊ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርና በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ናቸው::በሌሎች ቦታዎችም የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ተደራጅተው አባል ለመሆን ይችላሉ::የአለም አቀፉ ማኅበር ዋና ዋና ተግባሮች፡—

ሀ. ለአባል ማኅበራት ተገቢ መምሪያ መስጠት

ለ. ለአባል ማኅበራት ስራ ማከፋፈል

ሐ. የአባል ማኅበራትን ስራና ትግል ማቀናበር

መ. ከሌሎች የተማሪዎች ማኅበራትና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ከወደፊት ተራማጅ የተማሪ ማኅበራትና ሌሎች ድርጅቶች ጋር የትግል አንድነት መፍጠር

የአባል ማኅበራት ፕሬዚዴንቶች በኅብረት ማኅበሩን ይመራሉ::ብሄራዊው ማኅበር ለጊዜው ከመንግስት ከፍ ያለ ጭቆና ስለሚደርስበት በነጻ ከመስራት ታግዶአል::ስለዚህ የአለም አቀፉን ማኅበር ለጊዜው የሰሜን አሜሪካውና የአውሮፓው ማኅበር በኅብረት ይመራሉ::

## 2 ብሄራዊ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

ዩኒቨርሲቲው በሚገኝባቸው ከተሞች ያሉት ማኅበራት በኅብረት ያቋቋሙት ነው::ከነዚህ ከፍተኛውና ግንባር ቀደሙ አዲስ አበባ የሚገኘው ማኅበር ነው::ከብዙ አመታት ጀምሮ ብሄራዊው ማኅበር — በተለይ የአዲስ አበባው ማኅበር — በሚ

ወስዳቸው እርምጃዎች በኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ውስጥ ገንባር ቀደምትነቱንና ከሰራተኛውና ከገበሬው ወገን መሰለፉን አረጋግጠአል::በዚህም ምክንያት ከመንግስቱ ከፍ ያለ ጭቆና ይደርስበታል::እስከሁን ብዙዎች ተማሪዎች በመንግስቱ ፖሊስና የጦር ሰራዊት ተገድለዋል፣ተደብድበዋል፣በእስር ቤት ያለርህራሄ ተጉሳቁለዋል::ከነዚህ የፋሽስት ተግባሮች የመጨረሻው በታህሳስ 20 ቀን 1962 ኢ.ም. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት:የጓድ ጥላሁን:መገደልና ከዚያም ቀጥሎ የደረሰው እልቂት ነው::ከተገደሉት ሌላ ብዙዎች የማኅበር መሪዎች በእስር ቤት ይገኛሉ::

## 3 በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

ይህ ማኅበር ከተቋቋመ ከ15 አመታት በላይ ቢሆነውም የህዝቡን ወገን የመረጠውና ለትግል ታጥቆ የተነሳው ከ 1964 — እአአ — በኋላ ነው::ከዚያ ወዲህ ማኅበሩ ከወሰዳቸው አያሌ እርምጃዎች አንዳን ለመጥቀስ:— በ1969:እአአ:የፊውዳሉ መንግስት መሪ ኃይለስላሴ የበላይ ጠባቂዎቹን ቀና ከተማ:ዋሽንግተን:ለመሰለም በሄደበት ጊዜ የሰሜን አሜሪካው ማኅበር አደናቅፎት በሚገባው መንገድ የኃይለስላሴ አሳማ አገሪቱን መሸጥ እንደሆነ ለህዝብ አጋልጠአል::

ማኅበሩ በያመቱ ጠቅላላ ጉባኤ ያደርጋል::በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ በአመቱ ውስጥ የማኅበሩን ስራ ያካሄዳል::ማኅበሩ በብዙዎች የዩኒቨርሲቲ ከተሞች ቅርንጫፍ ማኅበራት አሉት::የቅርንጫፍ ማኅበራት ተግባር በንዴፊት ስለኢትዮጵያ ሁኔታ ማጥናትና መወያየት ሲሆን በሌላው ደግሞ ያሁኑን አገዛዝና የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም በተቻለ መንገድ ማጋለጥ ነው::ማኅበሩ "ቻሌንጅ" የሚባለውን የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መጽሄት ያዘጋጃል



## 4 በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

ከተቋቋመ አስር አመት ሆኖታል::ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ስለኢትዮጵያ ሁኔታ ሲወያይ ከቆየ በኋላ ከ1965ቱ —እአአ — የቪየና ጉባኤ ወዲህ ያሁኑ አገዛዝ ካልተለወጠ ለኢትዮጵያ ህዝብ ደህንነት ሊገኝ አለመቻሉን አረጋገጠ::ማኅበሩ ባለፉት አመታት በወሰዳቸው እርምጃዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ያለበት አስቃቂ ሁኔታና የሚያደርገው ትግል በአውሮፓ ህዝቦች በሰፊው ሊታወቅ ችሎአል::

የዚህ ማኅበር ከፍተኛ አካልና ውሳኔ ሰጭ አመታዊው ጉባኤ ሲሆን የአመቱን ስራ የሚያካሄድ ደግሞ በጉባኤው የሚመረጠው ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ነው::ጉባኤው የሚመርጠው የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ "ታጠቅ": እና "ትግላችን" የሚባሉትን የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መጽሄቶች ያዘጋጃሉ::"ታጠቅ" በአመት 2—3 ጊዜ ይወጣል::ጠለቅ ያሉ ቲዎሪዎችንና ሰፋ ያሉ ጥናቶችን ያዝላል::"ትግላችን" በየወሩ የሚወጣ የዜናና ጊዜያዊ ጥናቶችን የሚይዝ መጽሄት ነው::

ማኅበሩ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች በሚገኙበቸው የአውሮፓ አገሮች ሁሉ ቅርንጫፍ ማኅበራት አሉት::በያንዳንዱ ቅርንጫፍ ማኅበር ስር በየሀገሩ ልዩ ልዩ ከተማዎች የሚቋቋሙ ውስጣዊ ማኅበራት ሊኖሩ ይችላሉ::የቅርንጫፍ ማኅበራት ዋና ተግባሮች:—

ሀ. የተማሪ ማኅበራትን አላማዎች ለአባላት ማስታወቅና ማስረዳት

ለ. የአባሎችን የፖለቲካ ንቃትና የትግል መንፈስ ከፍ ለማድረግ:የትግል አንድነት ለማጥበቅ ልዩ ልዩ ጥናቶችን ማድረግ፣የጥናት ስብሰባዎች:ሰሚናር ... ማዘጋጀት

ሐ. ባገሩ ከሚገኙ የወደፊት ተራማጅ ድርጅቶች ጋር በመ

ተባበር የኢትዮጵያ ተማሪዎችን ትግልና በጠቅላላው የህዝቡን ትግል ማስረዳት

ዋና ዋናዎቹ ተግባሮች እነዚህ ናቸው፡፡ውስጣዊ ማኅበራትም በሉበት አካባቢ እነዚህኑ ተግባር ይፈጽማሉ፡፡

---

## አባል ለመሆን ትፈልጋለህን?

ወደአውሮፓ የሚመጡና በተማሪዎች ንቅናቄ በመሳተፍ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት በሚደረገው ትግል ከወገኖች ለመደባለቅ የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ምን ማድረግ አለበት?

1 በተቻለ ፍጥነት በሚገኝው አገር ካለው የቅርንጫፍ ማኅበር ወይም ባለበት ከተማ ከሚገኘው ውስጣዊ ማኅበር ሀላፊዎች ወይም አባሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ አለበት

2 የተማሪዎችን ንቅናቄ አላማዎች ጠንቅቆ ለመረዳት ችሰ ሰይል መጣርና ግልጽ ባልሆኑት ነጥቦች ላይ በሀገር ፍቅርና በቅን ልቦና በመመሬት ከማኅበሩ አባሎች ጋር መወያየትና መከራከር አለበት

3 በተማሪዎች ንቅናቄ አላማ የሚስማማና በትግሉ ውስጥ እሳተፋለሁ የሚል ሲሆን በየቅርንጫፍ ማኅበራት አዲስ አባላትን ስለመቀበል የወጣ የውስጥ ደንብ መሰረት አባልነት ጠይቆ መግባት አለበት

4 በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት በአባልነት ለሚገባ ወጣት ሁሉ የማኅበሩ ህግ የሚሰጠው ልዩ ልዩ መብቶችና ግዴታዎች ይኖራሉ

### ሀ የአባል መብቶች

1 ማንኛውም አባል የማኅበሩን መሪዎች የመምረጥና ለሀላፊነትም የመመረጥ መብት አለው



2 ማንኛውም አባል በየስብሰባው የመሳተፍ፡ሀሳብ የማቅረብና ድምጽ የመስጠት መብት አለው

3 ማንኛውም አባል ማኅበሩ በሚያዘጋጃቸው የባህል ተግባሮች የመሳተፍ መብት አለው

4 ማንኛውም አባል ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር በገጠመው ጊዜ ማኅበሩ በሚችለው እንዲረዳው የመጠየቅ መብት አለው

### ለ የአባል ግዴታዎች

1 ማንኛውም አባል የማኅበሩን አላማዎች በያጋጣሚው ማስወቅና መደገፍ፡ተቃዋሚዎችንም ማክሸፍና ማጋለጥ አለበት

2 ማንኛውም አባል በማኅበሩ ልዩ ልዩ አካሎች ስለአለምም ሆነ ስለኢትዮጵያ በሚደረጉት ጥናቶችና ልዩ ልዩ ፕሮብሌሞች በስራው መሳተፍ አለበት

3 ማንኛውም አባል ማኅበሩን ለማጠንከርና ዲሲፕሊን ለማስከበር ከልብ መጣር አለበት

4 ማንኛውም አባል የማኅበሩን አዱር በጊዜው መክፈል አለበት፡፡

---

## ጠቃሚ አድራሻ

በማንኛውም ጊዜ ስለማኅበሩ ጥያቄ ለማቅረብ ወይም ዜና ለመስጠትና ለማግኘት ብትፈልግ በሚቀጥለው አድራሻ መጻፍ ትችላለህ

በሚቀጥለው ገጽ ተመልከት

World-wide Ethiopian Students' Union

P. O. Box 3198

103 64 Stockholm

SWEDEN

---

የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪወች መጽሔቶች:—

"ታጠቅ" : "ትግላችን" : "ቻሌንጅ"

መጽሔቶችን አንብብ! አስነብብ! ተቸ! ተከራከር!



ትግላችን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸውና።

መሬት ላራሹ።

የሠራተኛው መብት ይጠበቅ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል።